የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# የምርጫ ዑደት

የምርጫ ዑደት ....................................................................................................................2
1. ቅድመ ምርጫ....................................................................................................................2
2. የምርጫ ዕለት ....................................................................................................................2
3. ድህረ ምርጫ ....................................................................................................................2
1. ቅድመ ምርጫ....................................................................................................................2
1.1 ዕቅድ ....................................................................................................................2
1.2 የምርጫ በጀት ....................................................................................................................3
1.3 የምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳ /Electoral Calendar) ዝግጅት.......................................................4
1.4 የመራጮችና የሰነዜጋ ትምህርት ....................................................................................................4
1.5 የምርጫ መረጃ ማሰባሰብና ማደራጀት....................................................................................................7
1.6 የምርጫ አስፈፃሚዎች ምልመላ እና ስልጠና ....................................................................................8
1.7 የምርጫ አስፈፃሚ አካላት ዝግጁነት....................................................................................................10
1.8 የምርጫ ቁሳቁስ ዝግጅት እና ህትመት....................................................................................................10
1.9 የመራጮች ምዝገባ....................................................................................................15
1.10 ዕጩዎች ምዝገባ....................................................................................................15
1.11 የምርጫ ክልል ማካለል....................................................................................................16
2. የምርጫ ወቅት ....................................................................................................18
2.1 የድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራና ውጤት አገላለጽ....................................................................................................18
2.2 የድምፅ መስጫ ቀን....................................................................................................19
2.3 የድምፅ ቆጠራ....................................................................................................19
2.4 ውጤት አገላለፅ....................................................................................................20
2.5 የቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት....................................................................................................20
3. የድህረ ምርጫ....................................................................................................22
3.1 ድህረ ምርጫ ግምገማ....................................................................................................22

## የምርጫ ዑደት

የምርጫ ዑደት ማለት ከቅድመ ምርጫ እስከ ድህረ ምርጫ ድረስ ያለውን አጠቃላይ የምርጫ እንቅስቃሴ የሚያካትት ነው። የምርጫ ዑደት በምርጫው ሥርዓት ምርጫ ከመጀመሩ በፊት የሚደረገው ዝግጅት ጀምሮ ውጤቱ እስኪታወቅና ይፋ ሆኖ ለአሸናፊዎቹ የአሸናፊነት ማረጋገጫ እስኪሰጥ ድረስ ያለውን ሂደት የሚያጠቃልል ነው።

**የምርጫ ዑደት ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች** ያቀፈ ነው። እነርሱም፡-

1. ቅድመ ምርጫ
2. የምርጫ ዕለት
3. ድህረ ምርጫ

## 1. ቅድመ ምርጫ

ቅድመ ምርጫ አብዛኛው የምርጫ እንቅስቃሴ የሚከናወንበት ወቅት ሲሆን ይህም ከምርጫ ቀን በፊት ያለውን ጊዜያት ያጠቃልላል። በቅድመ ምርጫ ወቅት የህግ ማዕቀፍ ዝግጅት፣ ማቀድ እና መተግበር፣ በጀት መመደብ፣ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዝግጅትና ምዝገባ፣ የምርጫ አስፈፃሚዎች ምልመላ፣ ሥልጠናና ምደባ፣ የምርጫ ክልል የማካለል ሥራዎች፣ የመራጮች ምዝገባ፣ ሥርዓተ ፆታ አሳታፊነት፣ የብዙሃን ማህበራት አሳታፊነት፣ የስነዜጋና መራጮች ትምህርት እና የመገናኛ ብዙሃን የሥራ እንቅስቃሴዎች በስፋትና በጥልቀት የሚሠሩበት ወቅት ነው።

### 1.1. ዕቅድ

ዕቅድ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ምሁራን በተለያዩ መንገድ ቢገለጽም መሠረታዊ ጽንሰ ሀሳብ ዕቅድ አንድ አካል ምን መሥራት እንደሚፈልግ የሚወስንበት አቅጣጫ እና በአመራር ሥርዓት ዓላማዎችንና ግቦችን ለመለካት የሚቻልበት የውሳኔ ሂደት ነው።

በሌላ በኩል ዕቅድ በቅድሚያ ዓላማን በመወሰን ወደ ምንፈልገው ግብ የሚያደርሰንን ዘዴ በመቀየስ ለሥራው የሚያስፈልገንን ሁሉ አሰባስቦ በማስተግበር የምንፈልገውን የምናይበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው።

የምርጫ የአፈፃፀም ዕቅድ የተቋሙ ስትራቴጂክ ዕቅድ አካል ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚፈጸሙ ተግባሮችን እንዴት እና በምን መልኩ በምርጫ አስተዳደር ወቅት እንደሚወሰን ከተጓዳኝ የምርጫ ህግ ጋር ተገናዝቦ የሚዘጋጅ ነው።

የምርጫ አፈፃፀም ዕቅድ ከምርጫው ተቋም ዓመታዊ ስትራቴጂክ ዕቅድ የሚወሰድ ይሆናል፡፡ የአፈፃፀም ዕቅድ ከምርጫ አስፈፃሚ ተቋሙ ስትራቴጂክ ዓላማ፣ ራዕይ እና እሴት መሠረት አድርጐ የሚቀረፅ ሲሆን በዋናነት አራት መሠረታዊ ጥያቄዎችን እንዲመልስ ይጠበቃል፡፡

እነሱም፡-

- አሁን የደረስንበት የት ነው?
- የት ለመድረስ እንደምንፈልግ?
- በምን መልኩ ቦታው ላይ መድረስ እንደምንችል? እና
- እንዴት እንደምንለካው ?

የሚሉትን የመለሰ መሆን ይገባዋል፡፡

የአፈጻጸም እቅድ ለበጀት ጥያቄ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ግብዓት ነው፡፡ የምርጫ ዕቅድ የሚዘጋጀው በምርጫ አፈጻጸም ላይ በሚሳተፉ ሰዎች አማካይነት ይሆናል፡፡ የአፈጻጸም ዕቅድ ዓላማን፣የሚሠራውን ሥራ፣ የሚፈለገውን ውጤት፣ የሰው ኃይልና አስፈላጊ በጀት፣ የአፈጻጸም የጊዜ ሰሌዳ እንዲሁም የአፈጻጸም ክትትልን ይጨምራል፡፡

## 1.2. **የምርጫ በጀት**

የምርጫ አስፈጻሚ አካል ባወጣው የምርጫ አፈጻጸም ዕቅድ የተቀመጡ ዓላማዎችና ግቦች ማሳካት የሚቻለው ለተቀመጠው ዕቅድ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገው በጀት ሲኖር ነው፡፡ ለአቅም ግንባታ ሥራዎች ከስልጠና እና ከምርጫ አስፈጻሚ አካላት ክፍያ፣ ከቁሳቁስ ግዥ እና አደረጃጀት ጋር ተያይዞ የሚሠሩ ክንውኖቹ በጀት ያሻቸዋል፡፡ በጀቱ ሲገኝም ክፍተቶችን በመዝጋት ምርታማ፣ ዉጤታማና ጥራቱን የጠበቀ የሀብት አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋትን ይጠይቃል፡፡

ለምርጫ አፈጻጸም የሚውል በጀት ለአንድ ሃገር መከላከያ፣ ትምህርት፣ እና የጤና ተቋማት ከሚውለው በጀት ጋር የሚመጣጠን እንደሆነ የተለያዩ ሃገራት ምርጫ አስፈጻሚ ተቋማት ጥናት ያሳያል፡፡ የምርጫ በጀት እጅግ ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቅ በመሆኑ በመንግሥት በጀት ምርጫ የሚያስፈጽሙ የምርጫ አስፈጻሚ ተቋማት የበጀት ችግር እንደሚገጥማቸው ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ የምርጫ በጀት በቅድመ ምርጫ በምርጫ ወቅት እና ከምርጫ በኃላ የሚያስፈልጉ የበጀት ጥያቄ የሚቀርብ ሲሆን በቅድመ ምርጫ የሚወጣ ገንዘብ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም የበጀት ጥያቄ በምርጫ ዓይነት እና በሚካሄደው ምርጫ ብዛት ላይ መሠረት ያደረገ ነው፡፡

ብዙ ሃገሮች ምርጫን በራሳቸው በጀት የሚያስፈጽሙ ሲሆን አንዳንድ ሃገሮች ደግሞ በዓለም አቀፍ ለጋሽ ሃገሮች ድጋፍ ወይም እርዳታ ያከናውናሉ፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የምርጫ በጀት እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ በመንግሥት በጀት አፈ,ቃቀድ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥር ቢሆንም ለሃገራዊ ዴሞክራሲ ግንባታ እና ለሰላም ባለው አስተዋጽኦ አንጻር ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ምርጫዎችን ለማስፈጸም በመንግሥት በጀት የሚመደብ ሲሆን ለአቅም ግንባታ ሥራዎች በተወሰነ ደረጃ ለጋሽ ድርጅቶች ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

**የምርጫ በጀት ዝግጅት ታሳቢ የሚሆኑ ጉዳዮች**

ለምርጫ ማስፈፀሚያ እንዲውል ታቅዶ የሚዘጋጅ በጀት መነሻ ከሚያደርጋቸው ጉዳዮች ዋና ዋናዎቹ ይመርጣል ተብሎ የሚገመት ሕዝብ ብዛት (የተገመተ የስታስቲክስ መረጃ)፣ የምርጫ ጣቢያ ብዛት፣ የምርጫ ክልል /ወረዳ/ ብዛት የዞን ብዛት፣ የምርጫ አስፈፃሚ ብዛት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዕጩ ብዛት ናቸው። እንዲሁም ቀድሞ ከተከናወነ ምርጫ የሚገኝ መረጃ ለቀጣዩ ምርጫ የበጀት ዝግጅት መነሻ ወይም ታሳቢ ሊሆን ይችላል። ከዚህም በተጨማሪ በጀት ሲዘጋጅ የምርጫ አስተዳደር አካል አዳዲስ ቴክኖሎጂ እና ዘመናዊ አሠራር እና የረዥም ጊዜ ስትራቴጂክ ግብ ግምት ውስጥ ማስገባት እንዲሁም የውጪ ተሞክሮዎችን መቃኘት ይገባል።

## 1.3. **የምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳ** (Electoral Calendar) **ዝግጅት**

የጊዜ ሰሌዳ የምርጫ ሥራ ሂደት ከቅድመ ምርጫ እስከ ውጤት አገላለጽ ድረስ የሚካተቱ ዝርዝር ተግባራት በጊዜ ከፋፍሎ የሚያሳይ እና በዋናነት የምርጫ አስፈፃሚ አካላት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሚዲያ፣ ሕዝቡ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚጠቀሙበት ሰነድ ነው። የምርጫ አስተደደር አካል ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ምርጫ ነፃ፣ ፍትሐዊ እና አሳታፊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ያዘጋጃል።

የምርጫ ሥራ በጊዜ የተገደበ በመሆኑ ሁሉም ተግባራት የሚከናወኑት በተቀመጠላቸው ጊዜ ውስጥ ነው። በዚህ መልክ የሚዘጋጅ የጊዜ ሰሌዳ የምርጫው መነሻ ቀን፣ የጊዜ ክፍፍልን፣ የፈጻሚው አካል ኃላፊነትን እና የድርጊቶች ትስስርን መግለጽ መቻል አለበት። በመሆኑም የጊዜ ሰሌዳ ለምርጫ ኦፕሬሽን ተመራጭ እቅድ መሆን ይችላል።

የጊዜ ሰሌዳው ሲዘጋጅ የሰነዶች ህትመት፣ የሰነዶች ድልድል፣ በሀገሪቱ የሚከበሩ በዓላትን፣ የሁሉንም ዜጐች ማህበራዊ እና ባህላዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል። ከዚህም ሌላ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳትና የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲ ምህዳሩን ለማስፋት የፖለቲካ ፓርቲዎች ዕጩዎችን ለማስመዝገብ እና የምርጫ ቅስቀሳ ለማድረግ የተመቻቸ ጊዜ እንዲያገኙ ታሳቢ በማደረግ መዘጋጀት ይኖርበታል። የምርጫ አስተዳደር አካላት ጊዜ ሰሌዳውን ሲያዘጋጅ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በመጋበዝ የማሻሻያ ግብአት እንዲሰጡ ያደርጋል።

ለምርጫው ስኬት ከባለድርሻ አካላት (ሚዲያ፣ የመራጮች ትምህርት፣ ብዙሃን ማህበራት፣ ታዛቢዎች) ጋር የሚደረጉ ውይይት፣ ሥልጠናዎችና መድረኮች የሚፈልጉት ጊዜ ታሳቢ ሊደረግ ይገባል። ምርጫውን የሚያስፈፅሙ በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚዎች ስልጠና እንዲሁም በየደረጃው የሚቋቋሙ የምርጫ ጽ/ቤቶችን በአግባቡ ለማደራጀት የሚያስፈልገው ጊዜ በትክክል ሊታይ ይኖርበታል።

## 1.4. **የመራጮችና የስነዜጋ ትምህርት**

ለዴሞክራሲ እሴቶች መጐልበት ዋነኛው መንገድ የስነዜጋና መራጮች ትምህርት ለዜጐች በጥራት፣ በስፋትና ተደራሽ በሆነ መልኩ መስጠት ሲቻል ነው። በምርጫ ሂደት ውስጥ በዕውቀት ያልዳበረ ሕብረተሰብ ምርጫውን በታለመው መልኩ ለማካሄድ እንቅፋት ሊሆን ይችላል። በመሆኑም ምርጫው በአግባቡ እንዲፈጸምና ውጤቱ ተቀባይነት እንዲኖረው ለስነዜጋና መራጮች ትምህርት ትልቅ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

### 1.4.1 *የስነዜጋ ትምህርት*

*የስነዜጋ ትምህርት ዜጎች ስለ መንግሥት አወቃቀር፣ ስለ ዴሞክራሲ ስርዓት፣ ስለ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት፣ ስለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸውና ግዴታዎቻቸው፣ ስለ ማህበራዊ ጉዳዮቻቸው፣ ስለአካባቢ ልማትና የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ሀገራዊ ዕውቀትና ግንዛቤ የሚያዳብሩበት የትምህርት ዓይነት ነው።*

*በህገ መንግሥቱ የተደነገጉት የዜጎች መብቶች በማንኛውም የመንግሥት አካል ቢጣሱ እንኳን ዜጎች በዚህ ትምህርት አማካኝነት መብትና ግዴታቸውን ለይተው የሚያውቁ እስከሆነ ድረስ መብቶቻቸውን ማስከበር ይችላሉ።*

*ዜጎች ህገ መንግሥቱ የሰጣቸውን መብት ተጠቅመው እየተሰባሰቡ ስለ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው፣ ስለ ማህበራዊ ኑሯቸው፣ ስለ መስተዳድር አካላት አገልግሎት አሰጣጥ ፣ ስለ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕቅዶቻቸው እንዲሁም በየደረጃው መርጠው ስለሾሟቸው/ስለወከሏቸው አካላት በስፋትና በጥልቀት እንዲወያዩ ከማገዝ አንጻር የስነዜጋ ትምህርት ከፍተኛ ድርሻ አለው።*

*የስነዜጋ ትምህርት ለዜጎች እንዲሰጥ የሚፈለገበት ዋናው ምክንያትም ዜጎች የሕዝብ ልዕልናንና የሥልጣን ባለቤትነታቸውን በሚገባ በመረዳት ህገ መንግሥቱን መሠረት አድርገው መብቶቻቸውን በማክበርና በማስከበር፤ እንዲሁም ግዴታዎቻቸውን በመወጣት በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታው ሂደት ውስጥ የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ለማስቻል ነው።*

### *ሀ. የስነዜጋ ትምህርት በተከታታይ መስጠት*

*የስነዜጋ ትምህርት ሳይቋረጥ በተከታታይ የሚሰጥ ከሆነ የዴሞክራሲ ፅንሰ ሃሳቦች፣ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች፣ የህገ መንግሥት ምንነትና ባህሪያት በህብረተሰቡ ዘንድ ይሰርፃል። እነዚህ ፅንሰ ሃሳቦች የታጠቀ ዜጋ (በአግባቡ የተረዳ ዜጋ)፦*

- *መብቱና ግዴታውን በአግባቡ ይወጣል፣*
- *በእኩልነት መመካከር፣ መወያየት እና መከራከር፣ ሂደቶች የመከታተልና የመገምገም፣ መቀጣጠርና መፍትሄ ላይ የመድረስ፣*
- *ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን ተገንዝቦ በሳል መፍትሄ ይሰጣል፣*
- *የመናገር፣ የመግባባት፣ የመገምገም፣ አቋም ይዞ የመከራከር ችሎታና ልምድ ያዳብራል፣*
- *የማህበራዊ ዕድገት ተሳትፎን ከፍ ያደርጋል።*

### *ለ. በስነዜጋ ትምህርት የባለድርሻ አካላት*

#### *ሚዲያ*

*የመንግሥት እና የግል የህትመትና ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች የመራጮች እና ስነዜጋ ትምህርት ብሎም የተለያዩ መረጃዎች ለህብረተሰቡ በማድረስ በኩል ያላቸው ሚና የላቀ ነው። ብዙ ሕዝብ ሬዲዮ ያዳምጣል፣ ቴሌቪዥን ያያል፣ ጋዜጣ ያነባል፣ ማህበራዊ ሚዲያዎች ይጠቀማል። እነዚህ ሰዎችም ያነበቡት እና ያዩት ለቤተሰቦቻቸው፣ ለጓደኞቻቸው … ያስተላልፋሉ። ስለሆነም ቦርዱ ከሚዲያ ጋር መልካም ግንኙነት ሊፈጥር ይገባል። ቦርዱ ከሚዲያ ጋር ያለውን ትስስር ለማጎልበት እና ማጠናከር ስትራቴጂ በመቀረፅ የስነዜጋ ትምህርት ብቻ ሳይሆን በሚያከናውናቸው ሥራዎች ሁሉ ህብረተሰቡ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ የሚያገኝበት ዕድል ማስፋት ይኖርበታል።*

ሚዲያው መረጃ ሲፈልግ ወዲያውኑ የተደራጀና ትክክልኛ መረጃ የሚያገኝበት ሁኔታ ሊፈጠር ይገባል። ሚዲያ ሲጠይቅ ብቻ ሳይሆን ሳይጠይቅም ቦርዱ መረጃ መስጠት አለበት። በቦርዱ የሚዲያ ማዕከል በማደራጀት የተለያዩ ፕሬስ ሪሊዝ፣ ፕሬስ ኮንፈረንስ….የሚዘጋጅበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል።

የምርጫ ዘገባ በባህሪው ከሌሎች ዘገባዎች የተለየ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የምርጫ አስፈጻሚው አካል በየጊዜው የሚሻሻል የመገናኛ ብዙሃን የምርጫ አዘጋገብ ደንብ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ማዋል አለበት። ለሚዲያ አካላትም የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያና የምክክር መድረኮች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ይህ ሲሆን ህብረተሰቡ ማግኘት የሚኖርበት ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ ማግኘት የሚችል ከመሆኑም በላይ ሚዲያዎቻችንም በመረጃ የበለፀገና ስል ምርጫ ጠንቅቆ የሚያውቅ ማህበረሰብ መፍጠር ይችላሉ።

**ሲቪክ ማህበራት**

የሲቪክ ማህበራት በሀገራችን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። በሀገራችን በሚካሄዱ ምርጫዎች ህብረተሰቡ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን፣ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ምርጫ እንዲያካሂድ ትምህርት እና ግንዛቤ በመስጠት ረገድ ያላቸውን አስተዋፅዖ ተኪ የሌለው መሆኑን ይታወቃል። ስለሆነም የምርጫ አስፈጻሚው አካል በስነዜጋ ዙሪያ የሚሰጠው ትምህርት እንደተጠበቀ ሆኖ የሲቪክ ማህበራትም ይህን ትምህርት በመስጠት ረገድ ሀገራዊ ግዴታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል።

### 1.4.2 **የመራጮች ትምህርት**

የመራጮች ትምህርት ምርጫ ሲቃረብ በእያንዳንዱ የምርጫ ሂደት ደረጃ በሚከናወኑ ተግባራት ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚሰጥ ትምህርት ነው። መራጩ ሕዝብ በመራጮች ምዝገባ ወቅት ሊያውቀው የሚገባውን መረጃ በቅድሚያ አውቆ እንዲመዘገብ፣ በግንባር ቀርቦ እንዲመርጥና የምርጫውን ውጤት እንዲከታተል በየደረጃው በስፋት መሰጠት ያለበት ትምህርት ይሰጠዋል። በምርጫ ሂደት ውስጥ በዕውቀት ያልዳበረ ሕብረተሰብ ምርጫን በታለመው መልኩ ለማካሄድ እንቅፋት ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ስለምርጫው ትክክለኛ ግንዛቤ ያላገኘ ህብረተሰብ በመራጮች ምዝገባ ወቅትና በአጠቃላይ በድምፅ መስጫው ዕለት ብዛት ያለው የድምፅ መስጫ ወረቀት ለዋጋ አልባነት ይዳርጋል። በምርጫው ሂደት ውስጥ በመራጮች ምዝገባ ወቅትና በድምፅ መስጫው ዕለት የሚደረጉ ሂደቶች ለምርጫው ውጤት ትልቅ ድርሻ ስላላቸው እንዲሁም የምርጫው ውጤት ተቀባይነት እንዲኖረው ለስነዜጋና መራጮች ትምህርት ትልቅ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። ይህም እንደየአገሩ ተጨባጭ ሁኔታ የምርጫ አስፈፃሚ ተቋም በመምራት የስነዜጋና መራጮች ትምህርት ከብዙሃን ማህበራትና የልማት አጋሮች ጋር በመተባበር በስፋት ሊሰጥ ይገባል። የፖለቲካ ፓርቲም የስነዜጋና መራጮች ትምህርት ከመስጠት አኳያ ትልቅ ሚና አላቸው።

### 1.4.3 **ባለድርሻ አካላት**

ባለድርሻ አካላት ማለት በተቋሙ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ አልያም ወይም ተቋሙ ራሱ ተጽእኖ ሊያሳድርባቸው የሚችሉ አካላት ናቸው። ተባባሪ አካላት የሚባሉት የቦርዱን ተልዕኮ መሳካት እነሱ ለቀሙለት ዓላማ መሳካት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋጽኦ ያበረክታል ብለው በማመን ተቋሙን የሚያስፈልገውን የቴክኒክ፣ የፋይናንስ እና የአቅም ግንባታ ድጋፍና ዕገዛ በመስጠት የሚተባበሩ እንደ የተባበሩት መንግሥታት የመሰሉ አካላት ናቸው።

በመሆኑም የውጭ ባለድርሻ አካላት የሚባሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የግል ተወዳዳሪዎች፣ ፌደራል መንግሥት፣ ሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት፣ ፌደሬሽን ም/ቤት፣ የፍትህ አካላት፣ የክልል መስተዳደሮች፣ ክልል ም/ቤቶች፣ የዴሞክራሲ

ተቋማት፣ መራጩ ሕዝብ፣ ሚዲያ፣ የሲቪክ ማህበራት፣ አዋኚዎች/ተመራማሪዎች፣ የሕዝብ ታዛቢዎች፣ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ታዛቢዎች ናቸው። በተመሳሳይ መልኩ ተባባሪ አካላት የሚባሉት ዩኒቨርስቲዎች (የሙያ ድጋፍ ስልጠና)፣ ሃገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ የተባበሩት መንግስታት (የፋይናንስ እና አቅም ግንባታ)፣ የአፍሪካ ሕብረት ኮሚሽን (የልምድ ልውውጥ መድረክ) እና ለጋሽ ድርጅቶች ናቸው።

## 1.5. የምርጫ መረጃ ማሰባሰብና ማደራጀት

ምርጫ በሚሊዮን የሚቆጠሩ መራጮችን የሚያሳትፍ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጨምሮ በርካታ ባለድርሻ አካላት በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተሳታፊ የሚሆኑበት በጣም ሰፊና ከፍተኛ ትኩረት የሚስብ ሀገራዊ ክንውን በመሆኑ በጥንቃቄ የተሰበሰበ፣ የተጠናቀረና የተደራጀ እና በወቅቱ ሥራ ላይ የሚውል መረጃ ያስፈልገዋል። በመሆኑም ለሁሉም የምርጫ ዓይነቶች ማለትም ጠቅላላ ምርጫ፣ የአካባቢ ምርጫ፣ የማሟያ ምርጫ፣ ለሕዝበ ውሳኔ እና ለድጋሚ ምርጫ ያለፈውን ምርጫ መሠረት በማድረግ መረጃ የማሰባሰብ፣ የማጠናቀርና የማደራጀት ሥራ ይሰራል።

የምርጫ አስተዳደር አካል የምርጫ መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ በፍጥነት ለህብረተሰቡ ለማድረስ፣ የምርጫ ውጤት ለመደመር፣ ለማጠናቀር እና በወቅቱ ለመግለጽ (ይፋ ለማድረግ) የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም ሊኖረው ይገባል። የምርጫ መረጃዎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በቅብብሎሽ በፍጥነት ከምርጫ ጣቢያ ወደ ማዕከል የሚመጣበትን አሠራር መዘርጋት ያስፈልጋል።

በዚሁ መሠረት መሰባሰብ እና በዘመናዊ የኢንፎርሚሽን ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም መደራጀት ካለባቸው መረጃዎች መካከል፡-

- በየደረጃው የተመለመሉ የምርጫ አስፈፃሚዎች ሙሉ መረጃ (ስም፣ አድራሻ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ስልክ ቁጥር...)
- የምርጫ ክልል፣ የወረዳ፣ የምርጫ ጣቢያ እና የቀበሌ ስምና ብዛት፣
- የተመዘገበ ድምፅ፣ የሰጠና ያልሰጠ ድምፅ ሕዝብ ብዛት (በጾታና በዕድሜ ተለይተው)፣
- የተበላሸ ወይም በትክክል ያልተሞላ የድምፅ መስጫ ወረቀት ብዛት፣
- በየምርጫ ጣቢያው ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች፣
- በምርጫ የሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሚያቀርቡት ዕጩ ብዛት፣
- በየደረጃው ያገኙት ድምፅ (ውጤት) በሀርድ ኮፒ እና ሶፍት ኮፒ ፎርማት በአግባቡ እና ተደራሽ በሆነ መንገድ ተደራጅቶ መቀመጥ ይኖርበታል።

በመላ ሀገሪቱ ያሉ በአዲስ መልክ በክልል መስተዳደሮች የተጨመሩ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ከተሞች እና ቀበሌዎችን መረጃ በክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አማካኝነት በማሰባሰብ፣ የማደራጀት ሥራ በማከናወን መረጃን ወቅታዊ (Update) ለማደረግ ቀጣይነትና ተከታታይነት ያለው ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

በሌላ መልኩ ለመራጩ ሕዝብ እና ሌሎች ደምበኞቹ በወቅቱ እና አመቺ በሆኑ መንገዶች ሁሉ መተላለፍ የሚገባቸው መልእክቶች እና መረጃዎች መለየት እና በአግባቡ መደራጀትና በወቅቱ ማስተላላፍ ያስፈልጋል።

## 1.6 **የምርጫ አስፈፃሚዎች ምልመላ እና ስልጠና**

የምርጫ ሥራ በጊዜ የተገደበ እና በርካታ የሰው ኃይል የሚፈልግ ነው። ይህንን የሰው ኃይል በቋሚነት ቀጥሮ ማሠራቱ ከፍተኛ ወጪ የሚያስከተል ከመሆኑም በላይ የአብዛኞቹ አስፈፃሚዎች ኃላፊነት በተወሰነ ጊዜ የሚገባደድ ነው።

በሀገራችን የምርጫ አስፈጻሚ አካል የምርጫውን ሥራ በቋሚነት እና በጊዜያዊነት ሠራተኞችን ቀጥሮ የሚያሠራ ሲሆን በምርጫ ወቅት በጊዜያዊነት ከሚያሠራቸው መካከል የምርጫ አስፈፃሚዎችና ጊዜያዊ የሰነድ ድልደል ሠራተኞች ይጠቀሳሉ። በተለይም በምርጫ ወቅት የምርጫ አስተዳደሩ አካል የምርጫ አስፈፃሚ በመመልመል እና በማሰልጠን ወደ ወረዳዎች እና ምርጫ ጣቢያ ያሰማራል።

### 1.6.1 **የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላ**

ምርጫ ነጻ፣ ሰላማዊ፣ ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ ተካሂዶ የሕዝብን አመኔታ እንዲያገኝ ከሚያስችሉ ነገሮች መካከል አንዱና ዋነኛው ምርጫውን በየደረጃው በተገቢው ሁኔታ ማስፈጸም የሚችሉ አስፈጻሚዎችን በከፍተኛ ትኩረት እና ጥንቃቄ መመልመል ሲቻል ነው።

### 1.6.2 **የምርጫ አስፈፃሚዎች ስልጠና**

ምርጫ ከመከናወኑ በፊት በቂና የተሟላ ስልጠና ለምርጫ አስፈፃሚዎች መስጠት ለምርጫው አፈፃፀም ስኬት በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነው። የምርጫ አስፈፃሚዎች ስልጠና ዓለም አቀፍ የምርጫ መርሆችን እንዲያውቁና እንዲተገብሩ ለማስቻል ሲሆን በዋነኛነት የምርጫ አስፈፃሚዎች ከዘመናዊ አሠራሮች፣ ከተሻሻሉ ህጎች ጋር እና እነሱን ተከትሎ ከሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር እንዲዋሃዱ እንዲሁም አዳዲስ ምርጫ አስፈፃሚዎች በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ በየጊዜው ስልጠና መሰጠት አለበት።

የምርጫ አስፈፃሚ አካል በየደረጃው ለሚገኙ የምርጫ አስፈጻሚዎች ስልጠና ለሚሰጡ የጽ/ቤት ባለሙያዎች፣ የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ባለሙያዎች በምርጫ ህግ ማዕቀፍ፣ በቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት፣ በዕጩዎች ምዝገባ አፈፃፀም፣ በመራጮች ምዝገባ፣ በድምፅ አሰጣጥ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ በምርጫ ማስፈጸሚያ በሰነዶች እና ቁሳቁስ አጠቃቀም እና በበጀት አመዳደብ እና አጠቃቀም በሚሉ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል።

የምርጫ አስፈጻሚዎች ቁጥራቸው ብዙ ስለሆነ ሁሉንም ሠልጣኞች በምርጫ አስተዳዳር አካላት ባለሙያዎች ብቻ ማሠልጠን አይቻልም። በመሆኑም የወረዳ/ምርጫ ክልል ምርጫ አስፈጻሚዎችን በየክልሉ ማዕከል በማሰባሰብ ማሠልጣኞቹ በተዋረድ ወደ ምርጫ ጣቢያ ወርደው የጣቢያ አስፈጻሚዎችን ያሰለጥናሉ። ሲያሰለጥኑ ወጥ የሆነ የአሠለጣጠን መንገድ እንዲከተሉ ሥልጠናውን በተቀረፀ ቪዲዮ እና ወጥ ሆኖ በተዘጋጀ የሥልጠና ማቴሪያል መጠቀም ይኖርባቸዋል።

### 1.6.3 የስልጠና ማኑዋል

የምርጫ አስፈጻሚው አካል ለምርጫው ሥራ አፈጻጸም የሚረዱ የተለያዩ መመሪያዎችን በየጊዜው የሚያዘጋጅ ቢሆንም ለሥልጠና ምቹ የሆኑ ለንባብ የሚቀል ወጥ የሆነ የሥልጠና ማኑዋል አዘጋጅቶ የምርጫ አስፈጻሚዎች እዲገለገሉበት ማድረግ ይገባል። ማኑዋሉ በክልል ቋንቋዎች ተተርጉመው የሚዘጋጅ፣ ለማንበብም ሆነ ሥራ ላይ ለማዋል የማይከብድ፣ የአስፈጻሚዎችን ግንዛቤ ለመለካት የሚያስችል በቂ መልመጃና የተግባራት ዝርዝር ቼክ ሊስት ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

### 1.6.4 የምርጫ ጣቢያ ማደራጀት

ምርጫ ጣቢያ በየደረጃው በሚካሄዱ ምርጫዎች ምዝገባ የሚካሄድበት መራጮች ድምፅ የሚሰጡበት እና የድምፅ ቆጠራ የሚካሄድበት ቦታ ነው። የምርጫ ጣቢያ ሲደራጅ መራጩ ሕዝብ ከአካባቢው ሳይርቅ ያለ እንግልት እና መጨናነቅ በጊዜው መርጦ እንድሄድ ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል።

የአንድ የምርጫ ጣቢያ መራጭ ብዛት በገጠር እና በከተማ የሕዝቡን ቁጥር መሠረት አድርጎ በምርጫ ህግ በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል። የምርጫ ጣቢያ አደረጃጀት መደበኛ እና ልዩ የምርጫ ጣቢያ በመባል ይታወቃ።

**ምርጫ ጣቢያ**

ምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ አስፈፃሚ ተቋማት ታችኛው የእርከን ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። ይሁን እንጂ ምርጫ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባ የሚከናወንበት፣ ድምፅ የሚሰጥበትና ቆጠራ የሚከናወንበት ብቸኛ ሥፍራ ነው። ስለዚህ ምርጫ ጣቢያዎች በሰው ኃይልና በቁሳቁስ በአግባቡ መደራጀት አለባቸው። በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሠረት አንድ የምርጫ ጣቢያ አምስት የምርጫ አስፈፃሚዎችን በአባልነት የያዘ ኮሚቴ ይኖረዋል። የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ኮሚቴውን በሰብሳቢነት ይመራል።

**ምርጫ ጣቢያ ሲደራጅ ትኩረት የሚሹ ሁኔታዎች፡-**

- ምርጫ ጣቢያው ለሕዝቡ (ለነዋሪው) ተደራሽ ወይም ቅርብ መሆን አለበት፣
- ለአካል ጉዳተኛ መራጮች ምቹ መሆን አለበት፣
- እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የሚያስተናግደው የመራጮች ብዛት ከ1500 መብለጥ የለበትም፣
- ምርጫ ጣቢያው ያለበት አካባቢ ለፀጥታ ምቹ መሆን አለበት፣
- በድምፅ መስጫው ቀን መራጮች ያለምንም መንገላታትና ሰልፍ በየምርጫ ጣቢያው ድምፃቸውን በተረጋጋ መልኩ እንዲሰጡ የሚያስችል መሆን አለበት፣
- የምርጫ ጣቢያዎች በጂኦግራፊክ ኢንፎርሜሽን ሲስተም (Geographic Information System) በመታገዝ በመራጭ ቁጥር እና ርቀት መሠረት ተከልለው የሚገኙበት አድራሻ በትክክል መታወቅ ይኖርባቸዋል።

**ልዩ ምርጫ ጣቢያ**

ልዩ ምርጫ ጣቢያ የሚቋቋመው ከምርጫ ክልላቸው ርቀው በካምፕ የሚኖሩ ወታደሮች፣ ሲቪል ሠራተኞች እና ቤተሰቦቻቸው፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ዜጎች፣ ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉ ዜጎች እንዲሁም በእስር ቤት የሚገኙ የመምረጥ መብታቸው ያልተገፈፈ ዜጎች በምርጫ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መራጮቹ በሚገኙበት ቦታ ወይም አካባቢ ነው።

## 1.7. **የምርጫ አስፈፃሚ አካላት ዝግጁነት**

በምርጫ ውስጥ በጣም አስፈላጊው የምርጫ አስፈፃሚ አካላት የሙያ ብቃትና ገለልተኛነት ነው። ለዚህም ምርጫውን በብቃትና በታማኝነት ለማካሄድ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ብቃት ባለው የሰው ኃይል፣ በቁሳቁስ፣ በፋይናንስ መጠናከር ይጠበቅበታል። በተለይም ከምርጫ አስፈፃሚዎች አኳያ የምርጫ አስፈፃሚዎች ምልመላና ስልጠና፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የድምፅ መስጫ ወረቀት፣ ሌሎች የምርጫ ቁሳቁስ ዝግጅትና ስርጭት እንዲሁም ከምርጫው በፊት የምርጫ አስፈፃሚዎች ስምሪት ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው።

ምርጫ በምርጫ አስፈፃሚዎች ብቃትና ገለልተኝነት ብቻ ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ከምርጫ አስፈፃሚዎች ጋር፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከብዙሃን ማህበራት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ለምርጫው ስኬትና ውጤታማነት በጋራና በትብብር መሥራት ይጠይቃል።

## 1.8. **የምርጫ ቅፃቅጽ ዝግጅት እና ህትመት**

ምርጫን የሚያስፈጽም አካል ምርጫን ነፃና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ለማስፈፀም በሚያደርገው ጥረት የምርጫ ቅፃቅጾች/ ሰነዶች/ በትክክል እንዲዘጋጁ እና እንዲሟሉ ማድረግ ይጠበቅበታል።

ከዕጩዎች እና መራጮች ምዝገባ ጀምሮ እስከ ውጤት አገላለፅ ያሉ የምርጫ ሂደቶች የየራሳቸው የሆኑ የተለያዩ ዓይነት ቅጻቅጾች ይኖራቸዋል። እነዚህ ቅጻቅጾች በአግባቡ ዲዛይን ካልተደረጉ እና በምርጫ አስፈጻሚው በጥንቃቄ ካልተሞሉ የተሟላ መረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ የምርጫውን ውጤት ተአማኒነት አጠያያቂ ሊያደርገው ይችላል።

### 1.8.1 **የቅፃቅጽ ዝግጅት (ዲዛይን)**

የምርጫ ማስፈፀሚያ ቅፃቅፆች ዲዛይን ሲደረጉ ቀላል፣ ያልተወሳሰቡ እና ግልጽ መሆን ይኖርባቸዋል። በመሆኑም የምርጫ አስፈፀሚዎች የቅፆችን ዓይነት እና አጠቃቀም በሚገባ ተረድተው በትክክል በመሙላት ምርጫው ግልጽ እና ታአማኒ እንዲሆን ለማስቻል ጥረት መደረግ አለበት።

**በቅፃቅፅ ዝግጅት ወቅት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች፦**

- የምርጫ ዓይነት በመለየት ተስማሚ ቅፃቅጾች ማዘጋጀት፣
- ባለድርሻ አካላትን ማወያየት እና ግብዓት መውሰድ፣
- በተለያዩ ክልሎች ተደራሽ ለማድረግ ቅጾችን በተለያዩ ቋንቋዎች የማስተርጎም ሥራ ማከናወን፣
- ቅጹ ሲዘጋጅ የቅጹን መጠን፣ ከለር እና የወረቀቱን ዓይነት መለየት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

### 1.8.2 **የሚዘጋጁ የቅፃቅጾች ዓይነቶች**

### **ሀ. የዕጩዎች ምዝገባ ቅጻቅፆች**

የእጩዎች ምዝገባ ቅጻቅጻች የሚባሉት ከግል እጩ ድጋፍ ማሰባሰቢያ ጀምሮ በግልም ሆነ በፖለቲካ ፓርቲ በእጩነት ለመወዳደር የሚያስችሉ ቅጻቅጾች ናቸው። ከእነዚህም ዋና ዋናዎቹ የድጋፍ ፊርማ ማሰባሰቢያ ቅጽ፣ የተጠቋሚ እጩዎች የሚመዘገቡበት ቅጽ፣ ተወዳዳሪ እጩዎችን ለሕዝብ ማሳወቂያ ፖስተር፣ የተወዳዳሪ እጩዎች ለቦርዱ ማሳወቂያ ቅጽ እና የእጩነት መታወቂያ ካርድ ወይም ቅጽ ናቸው።

### **ለ. የመራጮች ምዝገባ ቅፃቅፆች**

የመራጮች ምዝገባ ቅፃቅፆች ለመራጭነት ከሚያበቁ የመራጮች ካርድን ጨምሮ የመራጮች መዝገብ፣ በዕለት የተመዘገበ መራጭ መተማመኛ ቅጽ፣ መክፈቻና መዝጊያ ቃለ-ጉባኤዎች፣ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር ሪፖርት የሚደረግበት ቅጽን የሚያካትት ነው። በተጨማሪም በየደረጃው ለሚገኙ የምርጫ አስፈጻሚዎች እና ባለድርሻ አካላት የሚሰጡ ልዩ ልዩ መታወቂያዎችን ያጠቃልላል።

### **ሐ. የድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራ እና ውጤት አገላለፅ ቅፃቅፆች**

ለድምፅ  አሰጣጥ ቆጠራና ውጤት አገላለጽ የሚያገለግሉ የምርጫ ውጤት የሚሞላባቸው ቅጾች፣ ውጤት ለሕዝብ ማሰወቂያ ፖስተሮች፣ ድምፅ መስጫ ወረቀቶች እና እጩዎችን ለሕዝብ ማሳወቂያ ፖስተሮች፣ መቁጠሪያ ሰንጠረዥ፣ ቅሬታ መቀበያና ውሳኔ መስጫ፣ የቃለ ጉባኤ መያዣ ቅጽ፣ የምርጫ ሂደት ሪፖርት ማጠቃለያ ቅጽ፣ ለእጩ ወኪል የሚሰጥ የቆጠራ ውጤት መተማመኛ፣ የድምፅ መቁጠሪያ ሰንጠረዥ እና የተመራጭነት መታወቂያ ቅጾችን የሚያካትት ነው።

### 1.9.3 **ምርጫ ማስፈጸሚያ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ድልድል እና ስርጭት**

የምርጫ ማስፈጸሚያ ሰነዶችና ቁሳቁሶች እንደየምርጫው ዓይነት በወቅቱ ተቆጥረው፣ ተሰባጥረውና በአግባቡ ተደራጅተው በመደልደል በጥንቃቄ መሰራጨት ይኖርባቸዋል። በድልድልም ሆነ በስርጭት ጊዜ የሚፈጸም ማንኛውም መዘግየትም ሆነ ስህተት በምርጫው አፈጻጸም ላይ የራሱ ተጽዕኖ ማሳረፍ ስለሚችል በከፍተኛ ትኩረት መሠራት ያለበት ሥራ ነው።

### **የምርጫ ማስፈጸሚያ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ድልድል**

የሰነድ ድልድል የምርጫ ማስፈጸሚያ ሰነዶችንና ቁሳቁሶችን በሚፈለገው ቁጥር እና ዓይነት መለየት፣ መቁጠር፣ ማሰባጠር እና በአግባቡ መደልደልን ያካትታል። ምርጫ በባህሪው ሰፊና ተከታታይ ዝግጅት ሲደረግበት ቆይቶ በአንድ ቀን ድምፅ የሚሰጥበት ነው። በመሆኑም የሰነድና ቁሳቁስ ድልደላ ለበርካታ ምርጫ ጣቢያዎችና ቀበሌዎች የሚዘጋጅ በመሆኑ ሥራው በጣም ሰፊና ውስብስብ እንዲሁም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ይሆናል። ሰነዶቹ በጥንቃቄ


ተለይተው በሚፈለገው ቁጥርና ዓይነት ካልተደለደሉ በምርጫ ዕለት የሚያጋጥመው ችግር መጠነ ሰፊ እና ለማስተካከል ዕድል የማይሰጥ ነው።

የምርጫ ማስፈጸሚያ ሰነድ እና ቁሳቁስ ድልደል ሲከናወን፡-

- ብቃት ያለውና በቂ የሰው ኃይል መቅጠር፣ ማሰልጠን እና ማሰማራት፣
- የተሟላ የሰነድና ቁሳቁስ መረጃ ማሰባሰብና ማደራጀት፣
- ለምርጫ የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን ዝርዝር በመለየት በወቅቱ ማሟላት፣
- የምርጫ ሰነዶችና ቁሳቁሶችን በዓይነት፣ በቋንቋና በአድራሻቸው ለይቶ በጥንቃቄ በየሎጂስቲክስ መጋዘኑ ማከማቸትና ማደራጀት፣
- የምርጫ ሰነዶችን በጥንቃቄ እና በሚፈለገው ቁጥር መቁጠር እና ማሰባጠር፣
- ተሰባሪ፣ ፈሳሽ እና ቀለም ያላቸው የምርጫ ቁሳቁሶች ሲደለደሉም ሆነ ሲታሸጉ ለብቻቸው በጥንቃቄ መለየት እና ማዘጋጀት፣
- ሰነዶች በየጊዜያቸው (በዕጩ፣ በመራጮች እንዲሁም በድምፅ አሰጣጥ ወቅት) በተወሰነው ቁጥር መሠረት በአንድ ላይ ተጠርዘው ሲዘጋጁ (ሲደለደሉ) ፋይል አድርጎ ለማስቀመጥ እና በቀላሉ ለመለየት ያስችላል።
- እያንዳንዱ ሰነድ በምን ያህል ቁጥር እና ለየትኛው ምክር ቤት (ለቀበሌ ም/ቤት፣ ለወረዳ ም/ቤት፣ ለከተማ ም/ቤት፣ ለዞን ም/ቤት፣ ለክ/ከተማ ም/ቤት ለሕዝብ ተወካዮች እና ለክልል ምክር ም/ቤቶች) እንደሚደለደል በጥንቃቄ በመለየት በመከታተያ ቼክ ሊስት መሠረት መደልደል።
- የተደለደሉና በላስቲክ የታሸጉት ሰነዶችና ቀሳቁሶች በሌብሊንጉ መረጃ መሠረት በካርቶን በማስገባት ማሸግ፤ በካርቶኑ ላይ አድራሻ በጥንቃቄ መጻፍ፣
- የምርጫ ማስፈጸሚያ ሰነድና ቁሳቁስ ተደልድለው በታሸገበት በእያንዳንዱ ካርቶን ላይ ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ የምርጫ ጣቢያ ስምና ብዛት መጻፍ ይኖርበታል።
- የሚደለደሉ ሰነዶች በቼክ ሊስት መሠረት ያለጉድለት መደልደላቸውን እና በጥንቃቄ መታሸጋቸውን በተመለከተ ተገቢው የማያቋርጥ ክትትልና ቁጥጥር ማደረግ አለበት።
- የታሸጉትን ካርቶኖች በዞንና በምርጫ ክልል በመለየትና የሩቁን በማስቀደም ለሥርጭት በሚያመች መንገድ በቅድመ ተከተል ማከማቸት ያስፈልጋል።

ለአካባቢ ምርጫ የሚደለደሉ ሰነዶች በወረዳ፣ በቀበሌ፣ በምርጫ ጣቢያና እንደአስፈላጊነቱ በክፍለ ከተማ ሊታሸጉ ይችላሉ፡

*ቻርት 1-* **የምርጫ ማስፈጸሚያ የሰነድና ቁሳቁስ የድልድል**





**የምርጫ ማስፈጸሚያ ሰድና ቁሳቁሶች ስርጭት**

ማንኛውም የምርጫ ማስፈጻሚያ ሰነድና ቁሳቁስ ለታለመለት ዓላማ ስለማዋሉ በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚ አካላት የመከታተል እና የማስፈፀም ኃላፊነት አለባቸው። በመሆኑም የምርጫ ማስፈጸሚያ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ከማዕከል እስከ ምርጫ ጣቢያ ከመራጮችና ዕጩዎች ምዝገባ እና ከድምፅ አሰጣጥ ቀን በፊት መሰራጨት ይኖርባቸዋል። ሰነድ እና ቁሳቁስ ሲሰራጭ ደህንነቱ የተጠበቀ አስተማማኝ ማጓጓዣ መሰማራት ይኖርበታል፤ በሚጓጓዝበትም ወቅት ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል። ሰነዱን የያዘው ተሽከርካሪ በሚቆምበት በሚያድርበት እና በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ደህንነቱ

በአስተማማኝ ሁኔታ በተጠበቀ እና አመቺ ቦታ መሆን አለበት። ሰነዱ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ የምርጫ አስፈጻሚ አካል መኖር ያለበት ሲሆን የምርጫ ሰነዶችን ምርጫ አስፈጻሚ ለሆነ አካል ብቻ በጥንቃቄ ለይቶ ማስረከብ ይኖርበታል።

በአጠቃላይ የምርጫውን ሂደትና አፈጻጸም በፍትሐዊነትና ተደራሽ በሆነ መልኩ ለማዳረስ የሰነድ ስርጭቱ ለሩቅ አካባቢዎች ቅድሚያ በመስጠት የሚከናወን ሲሆን ተሰባሪ ለሆኑ ቁሳቁሶች ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። ከዚህም በተጨማሪ ሰነዱን በጊዜና በአግባቡ ከማሰራጨት ባለፈ የሰነድ ስርጭቱ ከማዕከል እስከ ምርጫ ጣቢያ ስለመደረሱ አስፈላጊ ክትትል መደረግ ይኖርበታል።

**ቻርት 2- የምርጫ ሰነድና ቁሳቁስ ሥርጭት**



## 1.10 **የመራጮች ምዝገባ**

በምርጫ ሂደት ውስጥ በትክክልና ሁሉ አቀፍ በሆነ መልኩ የመራጮች ምዝገባ ማካሄድ ለምርጫው ተአማኒነት መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ከዚህ አንፃር በሕግ ማዕቀፍ የመራጮች ምዝገባ ሂደት ውስጥ ያሉ መስፈርቶች እና ውጤቱ በትክክል መገንዘብ ያስፈልጋል።

የመራጮች ምዝገባ በምርጫ ሥራ ከተካተቱት ተግባራት መካከል በጣም ውስብስብና ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቅ በመሆን ይታወቃል። ስለ መራጮች ምዝገባ ሲታሰብ ቴክኒካል ሂደቶችን ብቻ ማሳብ ተገቢ አይደለም። ይልቁንም ሁሉን አቀፍ /holistic/ ፖለቲካዊ፣ አስተዳደራዊ እና ተግባራዊ ሂደቶችን ያቀፈ መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

የመራጮች ምዝገባ ጥራት የምርጫን ውጤት እስከ መወሰን የሚደርስ ከመሆኑም በላይ ይህንንም ተከትሎ በአንድ ሀገር የሚገኙ የዴሚክራሲ ተቋማት ላይም የራሱን ተጽዕኖ ማሳረፍ ይችላል። የመራጮች ምዝገባ ሂደት ግልጽና አሳታፊ ከሆነ በዴሞኪራሲ ላይ ያለው እምነት እየጎለበተ ይሄዳል።

በርካታ የመራጮች ምዝገባ ዘዴዎች ሲኖሩ አንዳንዶቹ ከሌሎቹ የበለጠ ወጪ ቆጣቢ፣ ቀላል ወይም ተዓማኒነት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። በመርህ ደረጃ የሚመረጠው የመራጮች ምዝገባ ሂደት ግልጽ፣ ውጤታማ፣ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ነው።

## 1.11 **ዕጩዎች ምዝገባ**

የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግል ዕጩ ተወዳዳሪዎች የምዝገባ መብታቸውን ያለ አድልዎ በእኩልነት በመጠቀም ጠንካራ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ፣ አማራጭ ሀሳቦችን ለሕዝብ እንዲያቀርቡና የዴሞክራሲ ባህልን እንዲያጎለብቱ እንዲሁም ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ተሳታፊ እንዲሆኑ የዕጩ ምዝገባ ይደረጋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጣዊ ዴሞክራሲ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ ጉን በምርጫ ሂደት አጠቃላይ ውጤት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ መፍጠር ይችላል። ስለሆነም ፖለቲካ ፓርቲዎች ዕጩዎችን ሲያቀርቡ በህግ ማዕቀፉ የተዘረዘሩ መስፈርቶች ማሟላታቸውን ማጣራት አስፈላጊ ነው። ከዚህም ባሻገር ውስጣዊ አሠራራቸውን በህገ ደንባቸው መሠረት ግልፅና አሳታፊ በሆነ መልኩ መተግበር ይጠበቅባቸዋል። በዕጩዎች አቀራረብ ወቅት ያለው አጠቃላይ ሂደት ግልፅና ሁሉ አቀፍ መሆን አለበት። የተወሰነውን ቡድን በማቀፍ ሌላው የሚያገል መሆን የለበትም።

የምርጫ አስፈፃሚ አካላትም ዕጩዎችን የሚያስተናግዱበት አሠራር ለተወዳዳሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነት የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ማድረግ እንዲችሉ የተመቻቸ ሜዳ መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በቅስቀሳ ወቅትም ፖለቲካ

ፓርቲዎች የምርጫ ህጐችንና የምርጫ ስነምግባር ተከትለው መንቀሳቀሳቸውን የምርጫ አስፈፃሚ ተቋም መከታተልና እያረመ መሄድ ይጠበቅበታል።

የተለያዩ የሕግ ማእቀፎች ማለትም የምርጫ ህግና መመሪያዎች በዕጩ አመዘጋገብ ስርዓትን በተመለከተ በአግባቡ ተዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውሉ ማደረግ ያስፈልጋል። በመሆኑም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሕጉ መሠረት ያለ አድሎና በእኩልነት በፖለቲካ ፓርቲ እና በግል ዕጩ ተወዳዳሪነት የመሳተፍ መብት አለው።

የምርጫ አስተዳደር አካል የዕጩዎች ምዝገባ ተግባራትን በአግባቡ ለማስፈጸም ይረዳው ዘንድ የዕጩዎች ምዝገባ ቅደመ ዝግጅቶችንና ተያያዥ ተግባራትን ያከናውናል። ለተወዳደሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የግል ተወዳዳሪዎች በዕጩ አቀራረብ፣ አመዘጋገብ እና ቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት ዙሪያ በወቅቱ ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል።

የምርጫ አስተዳደር አካል በምርጫ ለመወዳደር የተመዘገቡ የፖለቲካ እና የግል ዕጩ ተወዳደሪዎችን ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ መያዝ ይኖርበታል። ከዚህም ሌላ በምርጫ ክልል እና በምርጫ ጣቢያዎች የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል የዕጩዎችን ዝርዝር በመለጠፍ እና በመሳሰሉት ዘዴዎች ሕዝቡ ስለ ተወዳደሪ ዕጩዎች በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል።

የምርጫ አስፈፃሚ አካል ለዕጩ ምዝገባ የሚያገለግሉ ቅፆችና ሰነዶችን በሚፈለገው ቁጥርና ጥራት በማተም፣ በቂ የሰው ኃይል በማደራጀት፣ ሰነዶችንና ቁሳቁሶችን በጥንቃቄ በመቁጠር፣ በማሰባጠርና በመደልደል እንዲሁም በጊዜ ሰሌዳው መሠረት በወቅቱ በማሰራጨት የዕጩዎች ምዝገባ በወቅቱ ማካሄድ ይኖርበታል።

## 1.12 **የምርጫ ክልል ማካለል**

ምርጫ ክልሎችን በየጊዜው ፍትሀዊ እና ውክልናን ማረጋገጥ በሚችል መልኩ ማካለል የመራጮችን የድምፅ እኩልነት በማስጠበቅ የምርጫን ፍትሀዊነት እና ሰላማዊነት ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ከሚያረጋግጡ ተግባራት መሀከል አንዱ ነው። የምርጫ አስተዳደር አካል የምርጫ ክልል ማካለል ሲታሰብ ተገቢ ስልጠናዎች ለኃላፊዎቹ፣ ለሰራተኞቹ እና በማካለል ሂደቱ ውስጥ ለሚሳተፉ ወሳኝ ባለድርሻዎች መስጠት ይኖርበታል።

የምርጫ አስተዳደር አካል ምርጫ ክልል የማካለል ስራን በበላይነት የሚመራ ተቋም እንደመሆኑ የማካለል ሂደቱ የሚያካትታቸውን ዝርዝር ተግባራት አጥርቶ የመለየት፣ በግልጽ የማስቀመጥ እና ይህንኑ ለኃላፊዎች፣ ለሠራተኞች እንዲሁም ለባለድርሻዎች የማስገንዘብ፣ ወደ ሥራ ሲገባ የሂደቱ እርከኖች እንዲሁም የተሳታፊዎች ተግባር እና ኃላፊነቶች የሚወሰኑባቸው ደንቦች እና መመሪያዎች የማውጣት እና ተፈጻሚነታቸውን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት።

የምርጫ ክልሎችን የማካለል ሥራ እጅግ በጣም ውስብስብ፣ ብዙ ወጪ የሚያስወጣ እንዲሁም ረዘም ያለ ጊዜ የሚጠይቅ ሥራ ነው። ሥራው በሚሰራበትም ጊዜ የሀገሪቱ ማህበረሰባዊና ፖለቲካዊ ውስጣዊ ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ

ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት ይህንን ሥራ ለመሠራት እቅድ ሲያወጡ እና ስልቶችን ሲመርጡ የተለያዩ ከአስተዳደራዊ እና ከበጀት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን አስቀድመው በጥንቃቄ ማጤን ይኖርባቸዋል።

የምርጫ ክልሎችን የማካለል ሥራ በተለይ ባለ አንድ መቀመጫ የምርጫ ክልሎችን በሚጠቀም የምርጫ ስርዓት ውስጥ በየጊዜው እየተደጋገመ መሠራት ያለበት ስራ ነው። የማካለል ሥራው በተወሰነ ጊዜ ካልተደጋገመ በየምርጫ ክልሎች ውስጥ የሚገኘው የሕዝብ ብዛት ቁጥር ከፍተኛ ልዩነት እያሳየ ስለሚመጣ የውክልና ሚዛን ይዛባል፤ በመሆኑም የማካለል ሥራውን በየጊዜው እያከናወኑ የውክልና ሚዛንን ማስጠበቅ ያስፈልጋል። የምርጫ ክልሎችን ወሰን በየጊዜው እያስተካከሉ ማካለል ለወኪሎች (ተመራጮች) ብቻ ሳይሆን በየምርጫ ክልሉ ለሚኖረው መራጭ እንዲሁም የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ወሳኝ የሆኑ አንድምታዎች ያሉት ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ምርጫ በሚካሄድበት ጊዜ ሁሉ የምርጫው ውጤት ወይም የህግ አውጪው ምክርቤት የውክልና ስብጥር በምርጫ ክልሎች ወሰን መለዋወጥ ምክንያት የሚለያይ ይሆናል።

### የምርጫ ክልል የማካለል አለምአቀፍ መርሆች

የምርጫ ክልል የማካለል ሥራ በተለያዩ የምርጫ ስርዓት አይነቶች በእያንዳንዳቸው ውስጥ የተለያየ ውጤት ያስከትላል። ሆኖም ግን በየትኛውም ዓይነት የምርጫ ስርዓት ውስጥ ተግባራዊ ቢደረግ የምርጫ ክልል የማካለል ሥራ ሊያከብራቸው የሚገባ መርሆች አሉ። እነዚህም ከዓለም አቀፍ የምርጫ መመዘኛዎች መኃከል የድምፅ ክብደት እኩልነት (የእያንዳንዱ ሰው ድምፅ ክብደት እኩል መሆን) የሚለውን ለመተግበር የሚረዱ ይሆናሉ ማለት ነው። ዓለም አቀፋዊ የሆኑት የማካለል መርሆችም ጠቅለል ባለ መልኩ የሚከተሉት ናቸው፦

- ወካይነት፣
- የድምፅ ክብደት እኩልነት፣
- ሰጥቶ መቀበል እና አድኋዊ አለመሆን።

### የምርጫ ክልል ለማካለል ባለድርሻ አካላት

በአገራችን የምርጫ ክልል የማካለሉን ሥራ በበላይነት የሚመራው ምርጫው አስተዳደር አካል ሲሆን ሌሎች በርካታ ባለድርሻዎች የሚሳተፉበት ሰፊ ሥራ ነው።

የምርጫ ክልል ማከለል ባለድርሻ አካላት፡-

- የተወካዮች ምክር ቤት፣
- የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣
- ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት፣
- ማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣
- የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ድርጅት።

## 2. የምርጫ ወቅት

በምርጫ ዑደት (Electoral cycle) መሠረት በምርጫ ጊዜ በርካታ ወሳኝ ተግባራት ይከናወናሉ። የድምፅ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ፣ እንዲሁም የቅሬታ አቀራረብና አፈታት በዚህ ምዕራፍ የተካተቱ ርዕስ ጉዳዮች ናቸው።

### 2.1. የድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራና ውጤት አገላለጽ

የድምፅ መስጫ ቀን መራጩ በዲሞክራሲያዊ መንገድ ከቀረቡት ተወዳደሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የግል ዕጩዎች መካከል የሚፈለገውን የሚመርጥበት ቀን ነው። በአብዛኛው ሀገሮች የድምፅ መስጫ ቀን በአንድ ቀን የሚጠናቀቅ ሲሆን በአንዳንድ ሀገሮች ደግሞ በተለያዩ ቀናት ድምፅ እንዲሰጡ ይደረጋል።

በአብዛኛው ጊዜ የድምፅ መስጫ ቀን ሕዝቡ ነፃ ሆኖ ድምፅ እንዲሰጥ የእረፍት ቀን እና ከተለያዩ በዓላት ቀን ውጪ እንዲሆን ይደረጋል። እንዲሁም የድምፅ መስጫ ሰዓት ከጠዋቱ 12፡00 እስከ ምሽቱ 12፡00 ሰዓት ሊሆን ይችላል።

**ከድምፅ መስጫ ቀን በፊት ሊደረግ የሚገባው ጥንቃቄ**

- የምርጫ ጣቢያዎች ምቹ በሆነ አደረጃጀት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። እንዲሁም ድምፅ ሰጪው መራጭ ድምፅ የሚሰጥበትን ቦታ እንዲያውቅና ስለድምፅ አሰጣጡ አስፈላጊው ገለፃ ሊደረግለት ይገባል።

- በድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ፀጥታ አስከባሪዎች እንዲገኙ የማደረግ እና ኃላፊነታቸው እና ተግባራቸውን በዝርዝር እና በቅድመ ተከተል የማስገንዘብ ሥራ መከናወን ይኖርበታል።

- ለድምፅ አሰጣጡ ሂደት የሚያገለግሉ ድምፅ መስጫ ወረቀቶች እና ሌሎች ቁሳቁሶች በሚፈለገው ቁጥር እና ዓይነት መሟላታቸውን የማረጋገጥ ሥራ መከናወን ይኖርበታል።

- ለመራጩ ሕዝብ ስለድምፅ አሰጣጡ የአንድ ቀን ገለጻ የሚሰጥ ሲሆን ገለጻው የድምፅ መስጫ ወረቀት አጠቃቀም፣ አንድ መራጭ የሚመርጠው ዕጩ ብዛት የመወዳደሪያ ምልክቶቻቸውን

ትክክለኛ መጠሪያ በፖለቲካ ድርጅት የተወከሉና በግል ቀረቡ ዕጩዎች እያንዳንዱ እጩ ለየትኛው ምክር ቤት እንደሚወዳደር ያከታተ መሆን ይኖርበታል። በተጨማሪም መራጩ ሕዝብ በሚወዳደሩ ዕጩዎች ላይ ግንዛቤ ኖሮት በዕውቀት ላይ ተመስርቶ እንዲመርጥ የዕጩዎች ፖስተር በምርጫ ጣቢያዎች እና ሕዝብ በሚበዛባቸው አካባቢዎች መለጠፍ ይኖርባቸዋል።

- የድምፅ መስጫ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ከርክክብ ጀምሮ ውጤቱ ይፋ እስኪደረግ ድረስ ጥበቃና ጥንቃቄ ሊደረግላቸው ይገባል።

## 2.2. **የድምፅ መስጫ ቀን**

በምርጫው የሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግል ዕጩ ተወዳደሪ ወኪሎች፣ እንዲሁም የሕዝብ ታዛቢዎች የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ከመጀመሩ በፊት ስለድምፅ አሰጣጡ ሂደት ግንዛቤ በመፍጠር መግባባት ላይ መድረስ ያስፈልጋል።

በምርጫው ዕለት ድምፅ ሰጪው መራጭ ድምፅ እንዴት መስጠት እንዳለበት በተገቢው መንገድ ገለጸ ይደረግለታል። ከዚህም በተጨማሪ ድምፅ ሰጪው በነፃነት ድምፅ እንዲሰጥ ምቹ የሚስጥር ድምፅ መስጫ ክፍል ማዘጋጀት ይገባል። ማየት ለተሳናቸው እና ለአቅመ ደካሞች ቅድሚያ በመስጠት በመረጧቸው ረዳቶቻቸው አማካኝነት ድምፅ እንዲሰጡ ይደረጋል።

የምርጫው ሂደት ግልጽነት እንዲኖረው እና ጥርጣሬ እንዳይፈጥር ከፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች ጋር የተላከ የድምፅ መስጫ ወረቀት ብዛት፣ የድምፅ መስጫ ሳጥን እና ቁልፎች ኮድ ቁጥር በተመለከተ መተማመን ፈጥሮ መፈራረም ይገባል።

## 2.3. **የድምፅ ቆጠራ**

የድምፅ ቆጠራ የሚካሄደው ድምፅ በተሰጠበት ምርጫ ጣቢያ ሲሆን ከአቅም በላይ የሆነ አጋጣሚ ከተፈጠረ በምርጫ ክልል ሊቆጠር ይችላል። የድምፅ ቆጠራ ሲካሄድ የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል ዕጩ ወኪሎች እና ታዛቢዎች በግልጽ ቆጠራውን ማየት በሚችሉበት ቦታ ላይ መዘጋጀት ይኖርበታል።

የድምፅ ቆጠራ በሚከናወንበት ወቅት ሂደቱ የማይቋረጥ በመሆኑ ለቆጠራው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች እንደ ምቹ ጠረጴዛ፣ በቂ ወንበር፣ እስክርቢቶ፣ መቁጠሪያ ቅፅ፣ ብርሃን ሰጪ ቁሳቁሶች የመሳሰሉት አስቀድመው መሟላት አለባቸው።

ቆጠራው የሚከናወነው የመቁጠሪያ ሰንጠረዥ፣ ጭረት ወይም ታሊ በመጠቀም፣ ዘመናዊ የቆጠራ ሂደት በመከተል የድምፅ መስጫ ወረቀት ቆጠራው ግልጽ፣ ስህተት አልባ እና መተማመን የሚፈጥር መሆን አለበት።

የድምፅ ቆጠራ ውጤት ከተወዳደሪ ፖለቲካ ፓርቲ እና የግል ዕጩ ወኪሎች ጋር በመተማመን በመፈራረም ማሰረከብ ያስፈልጋል። ይህም ሁሉም ባለድርሻ አካላት በምርጫው ውጤት ላይ እምነት እንዲያሳድሩ ይረዳል።

የድምፅ ቆጠራውን ውጤት በተገቢው ቅፃ ቅፅ ላይ በጥንቃቄ በመሙላት ውጤቱን ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ ያስፈልጋል።

## 2.4. **ውጤት አገላለፅ**

ከማንኛውም ምርጫ ሂደት ዋና ዋና ግቦች አንዱ ውጤትን በአግባቡ አጠናቅሮ በወቅቱ በየደረጀው ለሕዝቡ ይፋ ማድረግ ይገባል። የምርጫ ውጤትን በጊዜው አለማሳወቅ አንዱ ጥርጣሬና የግጭት መንስኤ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም የምርጫ አስተዳደር አካል ከምርጫ ጣቢያ ጀምሮ ያለውን የምርጫ ውጤት በቅብብሎሽ እስከ ማእከል በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘዴ በመጠቀም ማሰባሰብ፣ ማደራጀትና ለሕዝቡ ይፋ ማድረግ ያስፈልጋል።

የምርጫ ውጤት ሲገለጽ፡-

- የተመዘገበ ሕዝብ ብዛት፣
- በጠቅላላ ድምፅ የሰጠ (voter turnout)፣
- በትክክል ድምፅ የሰጠ መራጭ፣
- ድምፅ ያልሰጠ መራጭ፣
- የተበላሸ የድምፅ መስጫ ወረቀት፣
- ዋጋ አልባ የድምፅ መስጫ ወረቀትን ማካተት ይኖርበታል።

የምርጫ ውጤት መግለፅ የሚችለው የምርጫ አስተዳዳር አካል ሲሆን ውጤት የሚገለጽበት ቦታ በምርጫ ጣቢያ፣ በምርጫ ክልል፣ በክልል/ከተማ አስተዳደር እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ይሆናል። ውጤቱ በፖስተር፣ በኤልክትሮኒክስና ፕሪንት ሚዲያ፣ በተቋሙ ድህረ ገጽ ለሕዝቡ ይፋ ይሆናል።

በአጠቃላይ የዚህ ማሽን አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ማሽኑን ዲዛይን በሚደርጉት፣ በሚያመርቱት፣ፕሮግራም በሚያደርጉት እና ሥራ ላይ በሚያውሉት ድርጅቶችና ግለሰቦች ብቃትና እውቀት ይወሰናል።

## 2.5. **የቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት**

የምርጫ አስፈጻሚ አካል (EMB) በምርጫ ሂደት የሚነሱ አለመግባባቶች በውይይትና በስምምነት ለመፍታት የሚያስችል የፓርቲዎች የጋራ መድረክ የማቋቋምና ማስተባበር እንዲሁም የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴዎችን በክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ በምርጫ ክልል እና በምርጫ ጣቢያ ደረጃ የማደራጀት ስልጣን ተሰጥቶታል። በዚህም መሠረት እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በሚመደብ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሰብሳቢነት የሚመራ

አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፤ ኮሚቴው ከሰብሳቢው በተጨማሪ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በምርጫ ክልሉ ከተመዘገቡ መራጮች መካከል የሚመረጡ፤ የማንም ፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆኑና በመልካም ሥነ ምግባራቸውና ሰብእናቸው የታወቁ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት አባላት ይኖሩታል።

**በመራጮች ምዝገባ ስለሚነሱ ክርክሮች**

ለምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይቀርባል፣ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በ፭ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሑፍ ይሰጣል። ለቀረበው አቤቱታ የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ አቤቱታ አቅራቢው ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ5 ቀናት ውስጥ አቤቱታ በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው። በምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የተሰጠውን ውሳኔ የተቃወመ ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሚቀርብ አቤቱታ ውሳኔ ከተሰጠበት በ5 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት። የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ይሰጣል። በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ እንደሆነ በ5 ቀናት ውስጥ ስልጣን ላለው በየደረጃው ላሉ የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ጉዳዩ እንዲታይለት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው። አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የቀረበለትን አቤቱታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል።

**በዕጩ ምዝገባ ስለሚነሱ ክርክሮች**

ለምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይቀርባል፣የምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሑፍ ይሰጣል። በምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በተሰጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ የፖለቲካ ድርጅት እጩ ወይም የግል እጩ በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ለሚቋቋም ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ5 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል። የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ሲቀርብለት በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሑፍ ይሰጣል። በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው። ችሎቱም የቀረበለትን አቤቱታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

**በድምፅ አሰጣጥ ስለሚነሱ ክርክሮች**

ለምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይቀርባል፣ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ጉዳዩን በማጣራት መራጩ ድምፁን እንዲሰጥ ሊወስን ይችላል፤ ወይም ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ በማድረግ ጉዳዩን ወደ ምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት በመላክ ውሳኔ እንዲያገኝ ሊያደርግ ይችላል። ጊዜያዊ ድምፅ የሰጠ መራጭ ከምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም እንደሁኔታው ስልጣን ካለው የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት የመምረጥ መብት እንዳለው የሚገልፅ ውሳኔ የድምፅ መደመሩ ከመጠናቀቁ በፊት ለምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት ካላቀረበ የሰጠው ጊዜያዊ ድምፅ ውድቅ ይደረጋል።

በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ቅር ጊዜያዊ ድምፅ የሰጠ መራጭ ወዲያውኑ ቅሬታውን ስልጣን ላለው የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል። ችሎቱም የድምፅ መዳመሩ ሂደት ውሳኔውን እስኪሰጥ ድረስ እንዲዘገይ ሊያዝ ይችላል።

# 3. የድህረ ምርጫ

ድህረ ምርጫ የምርጫ ወቅት የምርጫ ውጤት ይፋ ከሆነ በኋላ ቀጥሎ ያለው ጊዜ ሲሆን በዚህ ወቅት የድህረ ምርጫ ግምገማ፣ የምርጫ ክልል ማካለልና የተቋሙን እስተራቴጂካዊ ዕቅድ ዝግትና የመሳሰሉ ሰፋፊ ሥራዎችን ያካትታል።

## 3.1. ድህረ ምርጫ ግምገማ

የድህረ ምርጫ ግምገማ በዓለም አቀፍም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ በየወቅቱ የሚካሄዱ ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎች በትክክለኛው መንገድ በህገ መንግሥቱና በምርጫ ህጉ መሠረት መከናወናቸውን ወይም አለመከናወናቸውን ለማረጋገጥ ምርጫን በገለልተኛነት ለማስፈጸም ሥልጣን በተሰጠው አካል የምርጫ ውጤት ከተገለጸና አሸናፊው የፖለቲካ ፓርቲ ከታወቀ በኋላ በመላ ሀገሪቱ የሚካሄድ የዳሰሳ ግምገማ ጥናት ነው።

ጥናቱ የምርጫውን የአፈጻጸም ሂደት ከማሳየቱ ባሻገር በቅድመ-ምርጫ፣ በምርጫ ጊዜ በድህረ-ምርጫ ወቅት በተለያዩ የምርጫ ባለድርሻ አካላት ማለትም በመራጮች፣ በምርጫ አስፈጻሚዎች፣ በሀገር ውስጥ ታዛቢዎች፣ በፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች፣ በፍትህ አካላትና ሌሎች በምርጫ ጊዜ ጉልህ አስተዋጽኦ ባላቸው አካላት ዘንድ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ለመለየት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በጥናቱ መሠረትም የተለዩ ጥንካሬዎችን ይበልጥ አጠናክሮ በማስቀጠልና ድክመቶችን በማሻሻል ቀጣይ በሚካሄደው ምርጫ ላይ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን በመውሰድ ስኬታማ ምርጫ ለማስፈጸም ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

በሀገሪቱ የምርጫ ሕግና በወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫውን ውጤት ለሕዝቡ ይፋ ያደርጋል። በውጤቱ መሠረት በፖለቲካ ፓርቲዎች ያለመግባባት ውጤቱን በፀጋ ያለመቀበል ወይም ሌላ ቅሬታ ሊያስከትል ይችላል። ይህ ሁኔታ በሚከሰትበት ወቅት ግልፅ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት በየደረጃው ሊኖር ይገባል።

በአጠቃላይ በድህረ ምርጫ ግምገማ ከቅድመ ምርጫ ጀምሮ እስከየምርጫው ሂደት እስከ ሚጠናቀቅበት ያሉትን ጠንካራ ጐኖች ያጋጠሙ ችግሮች ትምህርት የተወሰደባቸው ጉዳዮች፣ እንዲሁም ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር የነበረው የሥራ ግንኙነት እና የነበሩ ተግዳሮቶች አንጥሮ በማውጣት ለቀጣዩ ምርጫ እራሱን የሚያዘጋጅበት ወቅት ነው።